ሰበር ዜና

አዲስ ፊልም ቤት ተከፈተ

አዲስ አበባ ውስጥ አዲስ ፊል ቤት ተከፈተ፡፡ ፊልም ቤቱ ቦሌ ዓለም ዐቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ይባላል፡፡ የሚያሳየው ፊልም «ሸኻት» የተሰኘ ሲሆን ሃያ አራት ሰዓት ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ እንግዶች ሲወጡ እንዴት እንደሚሸኙ፣ ሲገቡ ደግሞ እንዴት አቀባበል እንደሚደረግላቸው ያሳያል፡፡

ከዚህ በፊት ቦታው አውሮፕላን ማረፊያ በነበረ ጊዜ የመግቢያ ዋጋው 3 ብር ነበር፡፡ አሁን ግን መግቢያው አሥር ብር በመድረሱ ፊልም ቤት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህንን ፊልም ቤት ከሌሎች ልዩ የሚያደርገው አሥር ብር ከፍሎ የፊልሙ ተዋናይም ተመልካችም መሆን ስለሚቻል ነው፡፡

ከአሁን ጊዜ በኋላ ዕንባ እንጂ ገንዘብ የሌላቸው ሸኚዎች ከአጥር ውጭ የሚሰናበቱ ሲሆን፣ ዕንባ እና ገንዘብ ያላቸው ግን ወደ ውስጥ መግባት ይችላሉ፡፡ ከዚህ በፊት ተለያየን የተባለው ወንዝ ግሼን መንገድ ላይ ብቻ ይፈስ ነበር፡፡ አሁን ግን በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ እንደሚፈስ ያላቸውን ከሌላቸው እንደሚለይ ወንዙ ገልጧል፡፡

አንዳንድ ሸኚዎችም «ከእንግዲህ ከውጭ የሚመጡ ዘመዶቻችን እንድንቀበላቸው ከፈለጉ ተቀበሉን ብሎ መደወል ብቻ ሳይሆን የፊልም መግቢያውን ቀደም ብለው መላክ አለባቸው» ብለዋል፡፡ ሌሎችም የኢትዮጵያ ወዳጅ እንደሆነ ሃያ ሠላሳ ሆኖ ዘመድ መቀበል ልማዱ ነው፤ ካሁን በኋላ ግን አቀባበል በውክልና ሊሆን ይገባል» ሲሉ ነገሩን ተቀብለውታል፡፡